ማሳሰቢያ: ከዚህ በታች በቀረበው ሀሳብ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የነዚህ ኮሌጆች የሆነ ተማሪ በሙሉ የራሱን አስተዋጽዎ ማድረግ አለበት ።

መሻሻል አለበት የምትሉት ሀሳብ ካለ በኦንላይን Petition form ስለምናስሞላ ሀሳባችሁን በዛ ላይ ልታደርሱን ትችላላችሁ።

**ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለተማሪዎች አገልግሎት ጽ/ቤት ቢሮ ማቅረብ ያለብን ጥያቄ**

ጉዳዩ፡- ለተማሪዎች የሚሰጠው የምግብ እና የሌሎች አገልግሎቶች ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ስለመጠየቅ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ትምህርታችንን እየተከታተልን ያለነው ተማሪዎች በአንድ አንድ ኮሌጆች ውስጥ የሚሰጡ የተማሪ የምግብ አገልግሎቶች ጥራታቸውን አለመጠበቃቸውን እየገለፅን በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የተቋቋመ ቡድን እንዲከታተልልን እንላለን።

ጥራቱ የቀነሰ ምግብ ለተማሪዎች እየቀረቡ ያሉት ኮሌጆች፡

1. አራት ኪሎ የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ CNCS
2. ስድስት ኪሎ ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ College of Social Science
3. ቢዚነስ እና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ CoBE/FBE

በነዚህ ኮሌጆች ውስጥ ለተማሪዎች እየቀረቡ ያሉት የምግብ አገልግሎቶች ጥራቱ ያልተጠበቀ ምግብ ስለመሆኑ ተማሪዎች በየግዜው አቤቱታ ቢያቀርቡም ምንም አይነት ማስተካከያ ሊደረግበት አልተቻለም። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለተማሪዎቹ በቂ አገልግሎት ማድረግ እንደምችል ይታወቃል። የሀገሪቱ የኑሮ ደረጃ ምንም ያህል ዝቅተኛ ቢሆን የነገ ሀገር ተረካቢ ወጣት ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በተለያዩ በሽታዎች በመያዝ የተማረውን ትምህርት ወደ ተግባር ሳይቀይር በበሽታ መጠቃት ተገቢ አይደለም። ከነዚህ ሌሎች በተቀሩት በአዲስ አበባ ዩኒቨሲቲ ኮሌጆች ውስጥ ለተማሪዎች የሚቀርቡ የምግብ አገልግሎቶች ጥራታቸው የተጠበቀ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ባይባልም የተማሪዎቹ ጤንነት በተጠበቀ መልኩ ነው አገልግሎቱን እያገኙ ያሉት። ለምሳሌ ያክል ፡ በእንስሣት ጤና ኮሌጅ (College of Veterinary Medicine) ፣ በጤና ኮሌጅ (College of Health Science) ለታማሪዎች የሚቀርቡ ምግቦች በኮሌጆቹ ውስጥ የሚዘጋጁ ምግቦች ሲሆኑ ፤ የተበላሼ ምግብ ለተማሪ አይቀርብም። ይህ በእንዲህ እንዳለ ፤ በዋና ግቢ ፣ አራት ኪሎ ግቢ፣ የኢንጂነርንግ ግቢን ጨምሮ በኢኮኖሚክስ ግቢ ኮሌጆች እንጀራ ከውጭ ተገዝቶ እየገባ ነው። ይህ ተገዝቶ የምገባ እንጀራ እና ዳቦ፤ ግቢ ከገባ በኋላ እስኪያልቅ ድረስ ቢበላሽም ለተማሪዎች እየቀረበ ይገኛል። አብዛኛው ተማሪዎች የተበላሼ እንጀራ ወይም ዳቦ እየበላን ነው ቢለው ሀሳባቸውን አቅርበዋል። ግን ምንም የተስተካከለ ነገር የለም። በነዚህ ኮሌጆች ውስጥ የምማሩ ተማሪዎች በብዛት የጨንጓራ፣ የታይፎይድ፣ የታይፈስ፣ እና በመሰል በሽታዎች ታማሚ እንደሆኑ መረጃዎችን መጠቀም ወይም ምርምር ማድረግ ይቻላል። አብዛኛው ተማሪ በምግብ ጉዳይ ዙሪያ ጥያቄ ሲያነሳ የሚሰጠው ምላሽ መንግስት በአንድ ቀን 15 ብር ነው የበጀተላችሁ የምል ምላሽ ይሰጣል። የምበጀተው በጀት ይህ ከሆነ ፤ በአንድ ቀን ተማሪዎቹ እንደት 3 ግዜ ምግብ ሊመገቡ ይችላሉ የምል በተማሪዎች አይምሮ ውስጥ ጥያቄ እየፈጠረ ይገኛል። በዚህ ብር በየቀኑ ደረቅ እንጀራ እና ደረቅ ዳቦ ማስገባት ብቻል ፤ ወጡን ጨምሮ ሌሎቹ እንደት ሊሟሉ ቻሉ? እኛም ይህንን ጥያቄ ሲናነሳ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተማሪዎች አገልግሎት አስተዳደሮቹ ላይ ጥያቄ ለማንሳት ሳይሆን፤ መንግስት እንደ መንግስት ተማሪዎችን ማገልገል አልችልም የምል አቋም ካለው ተማሪዎቹ በቤሽታ እየተጠቁ በራሳቸው ላይ ዕዳ የሚሰበስቡበት ምንም አይነት ጉዳይ የለም። መስተካከል ካለበት ማስተካከል እና የተማሪዎችን ህይወት ለወደፊት ጤናማ በሆነ መልኩ ማስቀጠል። ይህ ካልተቻለ ደግሞ ተማሪዎቹ እንደ ግል ትምህርት ቤት እራሳቸውን ችሎ እየከፈሉ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት ። በእርግጥ በሀገራችን ውስጥ በተለያየ ምክንያት መንግስትን የተለያዩ የኢኮኖሚ ቀውስ ኢጋጥሞታል። ነገር ግን አሁን ለተማሪዎቹ አገልግሎቶችን

በጥራት ማቅረብ ያልቻሉ ዩኒቨርሲቲዎች በየዓመቱ ከሚበጀትላቸው በጀት አትርፎ ተመላሽ ሲያደርጉ ከዚህን በፊት ተገንዝበናል። በምግብ ጥራት የሚታወቁ ዩኒቨርሲቲዎችን መጥቀስ ይቻላል። አራማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ እና ሊሎችም ይኖራሉ። መንግስት መጠየቅ ካለበት በኢትዮጵያ ደረጃ ስለ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች መጠየቅ አለበት ብለን እናምናል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ግን በትምህርት ጥራት ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በልጦ በአገልግሎት ወደኋላ የሚቀርበት ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖርም። ነገ ይችን ሀገር ከችግሯ መታደግ የሚችለው ዛሬ በዚህ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሲቃዩን እያየ ያለው ተማሪ ነው። ይህ ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል። በእርግጥ ለሰው ልጅ በቅዲሚያ የሚያስፈልገው ጤናው ስለሆነ ነው እንጂ በጣም ብዙ ችግሮች በተማሪዎች ሰርቭስ ዙሪያ ይስተዋላሉ። ነገር ግን ያልተነሱ ችግሮች በሰው ጤና ላይ ችግር ስለማያደርሱ ተብሎ ይገመታሉ እንጂ እንደ አንድ ችግር ይጠቀሳሉ። ለምሳሌ፡ ለአካል ጉዳተኞች የሚሆን ደረጃውን የጠበቀ ለብቻ የተሰራ መኖርያ እና ሌሎችም የምገለገሉባቸው መሰረታዊ ነገሮች አለመኖር፣ የተማሪ ላውንቾች፣ 24 ሰዓት የሚሰራ ዲጅታል ላይበራሪ፣ በቂ የህክምና አገልግሎቶች፣ እንዲሁም ብዙ ውስብስብ ችግሮች ይጠቀሳሉ። የነዚህ ችግሮች በቀላሉ ማስተካከያ ያገኛሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ፤ ለተማሪዎች የምቀርበው የምግብ አገልግሎት ግን የሶስተኛ ወገን ቁጥጥር እና ክትትል ያስፈልጋል። ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ሲያስመርቅ እና ወደ ማህበረሰቡ ለአገልግሎት ሲልክ፤ ከነ ሙሉ ጤንነታቸው መሆን አለበት ። አለዚያ ሰዎችንም ሀገርንም መልሰን ወደ ችግር እየከተትን መሆናችንን መገንዘብ ተገቢ ነው።

በአሁኑ ሰዓት አንገብጋቢ ተብሎ የሚታይ ችግር ለተማሪዎች የምቀርበው ምግብ ሲሆን፤ አብዛኛው ተማሪዎች እንደምገልፁት የምግብ ፕሮግራሙ ራሱ ያልተመቻቸ እንደሆነ ይናገራሉ። የሌሎች ኮሌጆች የምግብ ፕሮግራም ከነዚህ ከሶስቱ ኮሌጅ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም መሻሻል ካለበት ከምግብ ፕሮግራምም ጭምር መሆን እንዳለበት ተማሪዎቹ ገልፀዋል።

የነበረው የምግብ ፕሮግራም

| ተ.ቁ | ቀን | ቁርስ | ምሳ | እራት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰኞ | ፍርፍር | ሽሮ/ምንቼት | የስጋ ወጥ |
| 2 | ማክ ሰኞ | ቂንጬ | ሽሮ/ምንቼት | የስጋ ወጥ |
| 3 | ዕሮብ | ማርማራታ | ሽሮ እና አትክልት(ድንች) | ሽሮ |
| 4 | ሀሙስ | ፍርፍር | ሽሮ/ምንቼት | የስጋ ወጥ |
| 5 | አርብ | ማርማራታ | ሽሮ እና አትክልት(ድንች) | ሽሮ |
| 6 | ቅዳሜ | ቂንጭጬ | ሽሮ | ሽሮ |
| 7 | ዕሁድ | እንቁላል/ ፍርፍር | 1 ሳምንት ፓስታ፤ 1 ሳምንት ሽሮ/ምንቼት | የስጋ ወጥ |

መሻሻል ያለባቸው ፕሮግራሞች

| ተ.ቁ | ቀን | ቁርስ | ምሳ | እራት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰኞ | ፍርፍር | ሽሮ/ምንቼት | የስጋ ወጥ በጥራት |
| 2 | ማክ ሰኞ | ሩዝ | ሽሮ/ምንቼት | የስጋ ወጥ በጥራት |
| 3 | ዕሮብ | ሞኮሮኒ/ፓስታ | ሽሮ እና አትክልት(ድንች) | ሽሮ |
| 4 | ሀሙስ | ፍርፍር | ሽሮ/ምንቼት | የስጋ ወጥ በጥራት |
| 5 | አርብ | ሞኮሮኒ/ፓስታ | ሽሮ እና አትክልት(ድንች) | ሽሮ |
| 6 | ቅዳሜ | ሩዝ | ሽሮ | ሽሮ |
| 7 | ዕሁድ | እንቁላል/ ፍርፍር | 1 ሳምንት ፓስታ፤ 1 ሳምንት ሽሮ/ምንቼት | የስጋ ወጥ በጥራት |

በቀላሉ የኢኮኖሚ ጉዳት ብዙም በማያስከትል መልኩ እናስተካክል ብባል በዚህ ፕሮግራም መሰረት እንዲስተካከል አብዛኛው ተማሪ ጠይቀዋል። ነገር ግን ይህ በቂ ነው ለማለት ሳይሆን፤ በጥራት ከተሰራ እና የተማሪዎቹ ጤንነት ከተተበቄ በሂደት ማሻሻያ እንዲያደርጉ ጥያቄ የምቀርብበት መንገድ ይመቻቻል። ከዚህ ጋር በተያያዜ ፤ የተማሪ ላውንቾች ጥራታቸው እየቀነሰ እና ከግቢ ውጭ ዋጋ ጨምሯል በምል ዋጋ እየጨመሩ ይገኛሉ። በነዚህ አገልግሎት ሰጪዎች ላይም ቁጥጥር ሊደረግልን ይገባል። በግቢ ውስጥ ለተማሪ አገልግሎት ተብሎ እስከ ገባ ድረስ የተማሪዎችን አቅም በተገናዘበ መልኩ እንጂ ጥራት ቀንሶ ዋጋ የምጨመርበት ምንም ዓይነት ድርግት ሊኖር አይገባም። ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይም ሀሳብ ሊነሳ የገባል። በሌላ በኩል አንድ አንድ አንድ ተማሪዎች የራሳቸውን ጥቅም ለማስቀጠል ላውንቾች የምያቀርቡት አገልግሎቶች በቂ ናቸው የምል ምላሽ እየሰጡ እንደሆነም እናውቃለን። እነዚህን እና መሰል ተግባር ፈፃሚዎችን እኛ አንቀበልም።

**የመፍትሔ ሀሳቦች:**

- ✓ የተማሪዎች ካፌ ምግቦች ሙሉ በሙሉ በግቢው ውስጥ የምዘጋጁ መሆን አለባቸው
- ✓ እንጀራ እና ዳቦ በግቢ ውስጥ መዘጋጀት አለበት።
- ✓ ከውጭ የምገቡ የምግብ ቁሳቁሶች ስለ ጤንነታቸው የሚከታተል የተማሪ ኮሚቴ መቋቋም አለበት
- ✓ ሽሮ፣ በርበሬ፣ ቅመማቅመም፣ ስጋ እና ሌሎችም የመሳሰሉት ከየት እንደምመጡ በተወከለው ኮሚቴ ጥብቅ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል።
- ✓ በተማሪዎቹ ምግብ ላይ ከፍተኛ ጥናት ሊደረግ ይገባል።
- ✓ ላውንቾቹ ጥራታቸው እና ዋጋቸው ለተማሪ የተመቻቸ ሁለታ ካልሆኑ ሌላ የምያገለግል አካል እንድገባ ሊደረግ ይገባል።

ይህ ሀሳብ እንደገና ኢዲት ተደርጎ ለተማሪዎች አገልግሎት ቢሮ መቅረብ አለበት ። የተማሪዎች አገልግሎት ቢሮ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ዓይነት መፍትሔ ካልሰጠ የበላይ አካል ጉዳዩን እንዲያስተካክል በሌላ ዶክመንታሪ ጥያቄ የምንቀርብ ይሆናል። ለዚህ ጥያቄ ተወካይ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆነ ተማሪ በሙሉ ሲለሆነ ፤ ይህ ችግር ስለመኖሩ እና እንዲስተካከል በጋራ መረባረብ ግድ ነው። ማንም ብቻኛ ተወካይ ሆኖ ስለዚህ ጉዳይ ጥያቄ የምያነሳበት ጉዳይ ሊኖር አይገባም።